# በቴዲ አፍሮ ስም ላይ ሌላ ድራማ

የወያኔ ዘረኛና አምባገነን ቡድን የኢትዮጵያን ሕዝብ በኃይል መግዛት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን፣ የኢትዮጵያን ተቋማት፣ ባሕል፣ ታሪክ እና እውቅ ኢትዮጵያውያንን መግደል፣ ማሰር፣ ማሰደድና ማዋረድ ማፈራረስና ማጥፋት ሥራዬ ብሎ ሲያካሂድ ቆይቷል። የኢትዮጵያን ስም ያስጠሩትን ታዋቂ ግለሰቦችን በተለየየ መንገድ ምክንያቶችን በመደርደር እየወነጀለ ፍርደ ገምድል ፍርድ ሲሰጥና ሲያጉላላ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል።

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በእስር ላይ ይሰቃያሉ። አንዳንዶቹ ለብዙ ዓመታት የት እንኳን እንደታሰሩ ቤተሰብም ሳያውቅና ሳይነገረው ከመሬት በታች ባሉ ድብቅ ማጎሪያዎች ታስረው የስቃይና የመከራ ኑሮ ይገፋሉ። በበሽታ እየተሰቃዩ ህይወታቸው የሚያልፈውም የዚያኑ ያህል ነው። ድብደባውና መንገላታቱ ተነግሮ አያልቅም። ይህ የብዙ ሺህ ኢትዮጵያኖች የዕለት ተዕለት ኑሮ ነው።

ቲዎድሮስ ካሣሁን ወይም ቴዲ አፍሮ የተባለው ወጣት አርቲስት ለሀገሩና ለወገኑ ፍቅር የገለጸባቸውን ዘፈኖች ወያኔ "ሕዝብ አፋቀረ" "ቀሰቀሰ" በሚል ጥላቻ ቴዲ አፍሮን የተቀነባበር ሴራ በማሴር ሰው "በመኪና ገጭተህ ገድለሃል" በሚል ክስሶ በሀሰት ምስክር በእስር ቤት እያንገላታው ነው። በዛሬው ዕለት ደግሞ ጥፋተኛ ነው የሚል በፍርደ ገምድሉ የወያኔ ካድሬ ተፈርዶበታል። በጣም ያሳዝናል። በሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸመው ድርጊት በዚህ ወጣት አርቲስት ላይም ደርሷል። እውነትና ፍትሕ ነጻ እስኪያወጡት ድረስ በእስር ቤት መንገላታት እና መሰቃየቱ ይቀጥላል። ለቴዲ አፍሮ ጥንካሬና ብርታቱን ሰጥቶት ነጻነቱን እንዲቀዳጅ እንመኛለን። ድጋፋችንን እናሰማለን።

በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለት ነገሮች ሊታወቁ ይገባል። ቴዲ አፍሮ ይፈታ ከሚለው አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄን የሚቃወም የለም። ሆኖም ግን ለፖለቲካ ጠቀሜታ ተቃዋሚ ነን በማለት የወያኔን እድሜ ለማራዘም የሚራወጡት "የሁለገብ ትግል" አራማጅ ነን ባዮችና ደጋፊዎቹ፣ እንዲሁም የአንድነት ፓርቲ ደጋፊዎች የቴዲን ጉዳይ ሊነግዱበት የፈለጉበት ምክንያት ማወቅ አለብን። ዋና ዓላማቸው ቴዲ ይፈታ የሚለውን ሲያቀነቅኑ በውነት ለቴዲ አፍሮ አዝነው ነው ወይስ ይኸው ለሕዝብ እየታገልን ነው እወቁልን ከሚል የአስመሳይነትና የግብዝነት መንፈስ? ደጋፊዎቻቸውስ የቴዲ ይፈታ መፈክራቸው ዋና የትግል መድረክ ማድረጋቸው የትግሉን መንፈስ፣ ትኩረትና አቅጣጫስ ለማስቀየር የታቀደ ይሆን? ከላይ በተላለፍ ትእዛዝ ወይስ የአጋጣሚ ነገር? ያጠያይቃል። በዋሽንግተን ዲሲ ለቴዲ አፍሮ ሰላማዊ ሰልፍ በወያኔ ኤምባሲ ፊት ለፊት ማድረጉ ለውጥ ያመጣል ብሎ ማሰብ የዋህነት ይመስለናል። ከዚህ በፊትም ታማኝ በየነ ከስድስት ጓደኞቹ ጋር ለካሜራ ቀራጩ ብቻ በሜጋፎን መፈክሮችን ለ10 ደቂቃ ቢያሰማም እውነት በዚያ ቴዲ አፍሮን ለማስፈታት ነበር ወይስ የዜና ሽፋን ለማግኘት? እንደ ወያኔ ድርጅት አባሎች የተነገራቸውን ብቻ የሚያደርጉት የነዚሁ የሁለት ድርጅቶች ደጋፊዎቻቸው በዲሴምበር ወር ሰላማዊ ሰልፍ በዋሽንግተን ዲሲ እና የጭፈራ ፓርቲ ዝግጅት በቫንኮቨር እያዘጋጁ መሆኑን ከበራሪ ማስታወቂያ አንበናል ሰምተናል። እዚህ ቫንኮቨር ውስጥ የቴዲ ምሽት 7435 Edmonds St. የኮሚኒቲ ሴንተር ውስጥ ፓርቲ ተደግሶ ሊበሉ፣ ሊጠጡ፣ በቴዲ ሙዚቃ ሊጨፍሩና የሚገኘው ገቢ ለአንድነት ፓርቲ ይሆናል ይሉናል በሬዲዮ ማስታወቂያቸው። ቴዲ እንዴት ነው የሚፈታው በዚህ ድርጊት? ከዚህ በላይ በቴዲ አፍሮ ስም መነገድ አለ እንዴ? ነገሩ ወዲህ ነው ወገኖች። ወያኔ በዚህ በዚህስ ጎበዝ ነው።

እንደሚታወቀው ለስንት ዓመታት እንኳን ለፍርድ በምን ምክንያት እንደተከሰሱ እንኳን ሳያውቁ በእስር ቤት የሚሰቃዩ ብዙ ኢትዮጵያኖች አሉ። የቴዲ ጉዳይ በመፋጠኑ እሰየው ቢባልም ከጀርባው የወያኔ ድራማ መኖሩን መዘንጋት የለብንም። ቴዲ አፍሮ ብዙ ዓመት ቢፈረድበት በሀሰት በመወንጀሉ ለሕዝብ ፍቅሩን በመግለጹ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ዝነኛና ተወዳጅ ያደርገዋል። ቢገድለው እንኳን ጀግና ሰማዕት ይሆናል። ወያኔ ያንን አይፈልግም። ወያኔ ቴዲ አፍሮ ላይ ብዙ ዓመት ፈርዶ ሲያበቃ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሽምግልና ይጀመራል። ቴዲ አፍሮ በዚህ በዚህ ጉዳይ ተስማማ ይባላል በሁኔታዎች ተገድዶ "ይቅርታ ጠይቆ ወጣ" ይባልና እንዲያውም "ወያኔን የሚደግፍ ተግባር ፈጸመ" ተብሎ በየሚዲያው በማናፈስ ቴዲ አፍሮን ከሕዝብ ለማጋጨትና ከሕዝብ ፍቅር ለማራቅ የሚደረግ ሴራ እንዳለ መገንዘቡ በጣም ጠቃሚ ነው። የወያኔን በህርይና ተግባራት መዘንጋት የለብንም። አሁን የሚያደርገውም ያንን ነው።

ሕዝባዊ ተቃውሞ ለማሰማት በወያኔ የንግድ ተቋማትና አገልግሎት ላይ በማደምና ባለመጠቀም መታገል አንደኛው መንገድ ሲሆን፡ ለምሳሌ በገናና በጥምቀት በዓል ወደ ኢትዮጵያ ባለመጓዝ ተቃውሚችንን ማስማት አንደኛው ነው። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሚሰቃዩትን ወገኖቻችንን እንዲፈቱና ይህ አምባገነን ዘረኛ ቡድን ከኢትዮጵያ እንዲወገድ በጽናት መታገል አለብን። ለቴዲ አፍሮና ለቤተሰቦቹ ብርታቱን ይስጥልን እያልን በቴዲ ስም መነገድና የበለጠ ጉዳት እንዳናደርስ መጠንቀቁ ተገቢ ነው። ትግላችን ይቀጥላል።

ተስፉ አበራ ከቫንኮቨር
ዲሴምበር 1 ቀን 2008